ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
2017/29

ለበለጠ መረጃ በ011-130-7033 ይደውሉ
http://et.usembassy.gov ይጎብኙ

የአሜሪካ ኤምባሲ የፕሬዚዳንት ጆን ኤፍ ኬኔዲን 100ኛ የልደት በዓል የሚዘክር የፎቶ ዓውደ ርዕይ በማዘጋጀት ለባህርዳር ወጣቶች የላቀ አስተዋጽኦ ክብር ይሰጣል

ባህርዳር፤ ኢትዮጵያ፤ ጥቅምት 1, 2010 ዓ.ም፡ - የአሜሪካ ኤምባሲ ከባህርዳር ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር የቀድሞ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የጆን ኤፍ ኬኔዲን 100ኛ የልደት በዓል የሚዘክር የፎቶ ዓውደ ርዕይ አዘጋጅቷል፡፡ የፕሬዚዳንት ኬኔዲን ህይወትና ሥራዎች የሚዘክረው የፎቶ ዓውደ ርዕይ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከበረው የፕሬዝዳንቱ 100ኛ የልደት በዓል አካል ሆኖ፤ በባህርዳር ገነሜ የሕዝብ ቤተመጽሐፍ ውስጥ በሚገኘው የአሜሪካ ማዕከል ከጥቅምት 1-8, 2010 ዓ.ም ድረስ ለህዝብ እይታ ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡

በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ማይክል ሬይነር በፎቶ ዓውደ ርዕይ መክፈቻ ላይ፤ የኢትዮጵያ ወጣቶች የተሻለ ነገን እንዲያሳኩ ለማስቻል ሀገራቸው እያከናወነች ያለውን ሥራዎች ላይ አጽንኦት የሰጠ ንግግር አድርገዋል፡፡ አምባሳደሩ አክለውም፤ በፕሬዝዳንት ጆን ኤፍ ኬኔዲ አነሳሽነት የተመሰረቱት የሰላም ጓድ እና የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (USAID) በኢትዮጵያ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ፤ የፕሬዝዳንቱ ሥራዎች ዘመን ተሻጋሪ እና ቀጣይነት እንዲኖራቸው ማድረጋቸውን ተናግረዋል፡፡

አምባሳደር ሬይነር በንግግራቸው በተለይም በቅርቡ የተጠናቀቀውን እና ለ240 የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ሴት ተማሪዎች የኮምፒዩተር ሳይንስ ክህሎትን ለማዳበር በአምስት የኢትዮጵያ ከተሞች ሲሰጥ የቆየውን Girls Can Code የመሳሰሉ ስልጠናዎች ያላቸውን ጠቀሜታ አፅንኦት ሰጥተው አውስተዋል፡፡ ከአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት መርሀ ግብሮች አንዱ እና እድሜያቸው ከ15-29 ለሆኑ ሥራ አጥ የገጠር ወጣቶች ገቢያቸውን እና የኢኮኖሚ አቅማቸውን ማዳበር የሚያስችለው "የወጣቶች አቅም ግንባታ" መርሀ-ግብር፤ በአምባሳደሩ ንግግር ከተጠቀሱት ውስጥ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም፤ በአሜሪካ መንግሥት አማካይነት ቀጣይ የአፍሪካ መሪዎችን መፍጠር ላይ የሚያተኩረው የወጣት አፍሪካውያን መሪዎች ጅማሮ መርሀ ግብር (YALI) በአምባሳደሩ ንግግር ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች አንዱ ነበር፡፡ የዛሬው መርሀ-ግብር፤ እ.አ.አ. በ2018 ለሚካሄደው እና አሸናፊዎች በአሜሪካ ለስድስት ሳምንታት የሚቆይ የቀለም ትምህርት እና የአመራር ክህሎት ስልጠና ዕድል፤ እንዲሁም የአፍሪካ ቀጣይ መሪዎች የእርስ በርስ ትስስር እንዲፈጥሩ ለሚያስችለው የማንዴላ ዋሽንግተን ፌሎውሽፕ ማመልከቻ የመጨረሻ ቀን ጋር ተገጣጥሟል፡፡

የባህርዳር ዩኒቨርስቲ የዝግጅቱ አካል የሆነ እና የፕሬዝዳንት ጆን ኤፍ ኬኔዲን ሥራዎች ለማስቀጠል ያለመ፤ በበጎ ፈቃደኝነት፤ ሳይንስና ቴክኖሎጂ፤ ትምህርት እና ሥራ ፈጠራ ላይ ያተኮረ የወጣቶች ኮንፈረንስ እና የፓናል ውይይት ለጥቅምት 2, 2010 አሰናድቷል፡፡

የፎቶግራፍ ዓውደ ርዕዩ በባህርዳር ከተማ ከታየ በኋላ፤ በሐዋሳ፤ ጂማ እና ድሬዳዋ ከተሞች በመዘዋወር ለህዝብ እይታ ክፍት ሆኖ የሚቆይ ሲሆን፤ በመጨረሻም፤ በዘላቂነት ወደ ሚታይበት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲው የጆን ኤፍ ኬኔዲ ቤተመጻሕፍት ይመለሳል፡፡

በብሩክሊን ማሳቹሴትስ እ.አ.አ. በግንቦት 29፤ 1917 የተወለዱት ፕሬዝዳንት ኬኔዲ፤ በዕድሜ ወጣቱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የነበሩ ሲሆን፤ በተለይም ለትምህርት፤ ወጣቶችን ለሀገራቸው እንዲሰሩ በማበረታታት እና ሰውን በጨረቃ ላይ ለማሳረፍ በነበራቸው ትልቅ ህልም ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ይታወቃሉ፡፡

የፕሬዝዳንት ኬኔዲ የስልጣን ዘመን በአሜሪካ ወርቃማው የፎቶ ጋዜጠኝነት ዘመንም ነበር፡፡ እ.አ.አ. በ1946 ለአሜሪካ የምክር ቤት አባልነት መወዳደር ከጀመሩበት አንስቶ፤ ከጃኩሊን ኬኔዲ ጋር እ.አ.አ. በ1953 የፊጸሙት የተረት ዓለም የሚመስል ጋብቻ፤ እ.አ.አ. በ1960 ወደ ዋይት ሀውስ ለመግባት የነበረው ሂደት፤ እንዲሁም የጦር ሃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹምነት እና የ1963ቱን አሰቃቂ ግድያ ጨምሮ ፕሬዝዳንት ኬኔዲ በርካታ ፎቶግራፎችን በመነሳት ተወዳዳሪ ያልተገኘላቸው ፖለቲከኛ ነበሩ፡፡

የኬኔዲ ፕሬዝዳንታዊው ቤተመጽሐፍ እና ሙዚዬም 100ኛውን የልደት በዓል ምክንያት በማድረግ በመላው አሜሪካ አዲሱን ትውልድ በማነቃቃት፤ ድፍረት፤ ነጻነት፤ ፍትህ፤ የአገልጋይነት መንፈስ እና ራዕይ የመሳሰሉ የእርሳቸው ዘመን ጠቃሚ እሴቶችን ትርጉም እንዲረዱ ለማስቻል ተከታታይ ሁነቶችን ያዘጋጃል፡፡ ዓውደ ርዕዩ በአሜሪካ ዋሽንግተን በከተማ ደረጃ ከጆን ኤፍ ኬኔዲ ፐርፎረሚንግ አርትስ፤ ከስሚዞንያን ብሔራዊ የስዕል ማዕከል እንዲሁም ከስሚዞንያን ብሔራዊ የታሪክ ሙዚየም እና ከዋይት ሀውስ የታሪክ ማህበር እና ኒውዚዬም ጋር በጥምር ይከበራል፡፡

###